# ለኢትዮጲያ ሕዝብ መሪውንና ድርጅት የሚመርጥለት ማንነው?

## ከአንድነቱ መንደር ከቃራ 3

ከርእሱ መጠይቅ ተነስቼ መጣጥፌን እንድጭር የተገደድኩበት መንስኤ ከፖለቲካው አካሔድ ከምናየው ክስተት በመነሳት በአካልና በስልክ ጭውውቶችና ንግግሮች ወቅት ያስተዋልኩትንና እየተንፀባረቀ ያለውን መሰረት ያደረገ ነው።

ዶክተር አገሌና አቶ አገሌ ምሁር ስለሆኑ ወይዘሮ አገሊትንና አቶ ዳሽን ጨምሮ ዴሞክራሲን በሀገራችን ውስጥ ያመጣሉ ብዬ ስለማምን መሪ እንዲሆኑ እደግፋቸዋለሁ በማለት በአንዳንድ ወገኖች የሚቀርበው ሃሳብ ባዶና የተንሸዋረረ እይታ መሆኑን ለማሳየት ሲሆን እነዚህ ሃይሎች የፈለጉትን የመደገፍ መብታቸው የተጠበቀ ሆኖ ጉዳዩ የሃገራችንና የህዝባችን ጉዳይ በመሆኑ በዜግነት በቀጥታ ስለሚመለከተን የዚህን አመለካከት ስህተትና ጎጂ ባህርያቱን ለማመልከት ተቃውሞዬን ስጀምር፣

የስልጣን ባለቤትና መብት የኢትዮጵያ ህዝብ ብቻ መሆኑ እየታወቀ የዚህ አላማ አራማጅ ግንባር ቀደም መሪዎች በውጪ አገር በመኖራቸው በኢኮኖሚና በቴክኖሎጂ ያደጉ ሃገሮች ከደረሱበት የስልጣኔና የእውቀት ደረጃ ላይ በመነሳት ነጮቹ የሚያንጸባርቁትን ያደገና የዳበረ የዴሞክራሲ ጥያቄዎችንና የ 21ኛ ክፍለ ዘመን አስተሳሰባቸውን የያዙ መጻህፍቶችን ገልብጠና ሸምድዶ ስሜትን የሚኮረኩርና አስደሳች ሃሳቦችን ለቅሞ በማውጣት መናገር መቻል ብቻውን ያለ ጠንካራ ድርጅት ታግሎ የማታገል ብቃት ከቀራጥነትና ከመስዋእትነት ውጪ በወሬ ብቻ የኢትዮጵያን ህዝብ ከአምባገነንና የብረት አገዛዝ ነጻ ማውጣት ይቻላል ብሎ ማሰብ በራሱ አለማወቅ ሲሆን አሊያም ማፍረስ ነው።

ጥቂቱ ለአብላጫው ውሳኔ መገዛት የዴሞክራስያዊ አካሄድ መግለጫው ሆኖ ዲያስፖራው በሃገር ቤት ብዙሃኑ ህዝብ የደገፈውን ድርጅት የጀርባ አጥንት ሆኖ ሁለገብ የዜግነት እርዳታውን ከማበርከት ውጭ ትግሉን በርቀት ሆኖ በኤሌክትሮንክስ መሳሪያ መምራትና ኢዴሞክራሲያዊ አካሄድ ተከትሎ መሪና ለህዝብ የሚሆን ድርጅት መምረጡ እውነተኛውን የህዝብን ትግል የሚጎዳ አደገኛ ሃሳብ ነው።

የአንጃው ፈጣሪዎች ግንዳቸውና መሰረታቸው በውጪ በአሜሪካንና በአውሮፓ ሆኖ የዚህ ቡድን አንዱ ክንፍ በሐገር ቤት የሚንቀሳቀስ ስለሆነ አካሄዳቸው የመንትዮሽ መንገድ ስለተከተለ በሁለት ክፍሎ ማየት የግድ ይላል።

1. በውጪ ያለው አንጃ.......ይህ መሪዎችንና ዋንኛዎቹን አንቀሳቃሾች ያያዘው የአንጃው ከፍተኛው የአመራር ክፍል መቀመጫውን በባእድ አገር አድርጎ የሀገር ቤቱን ትግል በርቀት ሆኖ
የሚቆጣጠር ሃይል ነው።

በውጪ የሚኖሩ የኣንጃው ደጋፊዎች ስብጥርን በተመለከተ ከጥቂቶች በስተቀር በኣብዛኛው በዙሪያው ያሰባሰባቸው የወያኔ አገዛዝን የሚደግፉ በስርዓቱ የጥቅም ተካፋዮችና የወደፊት የካሬ ሜትርና ጥቅማጥቅም ዓላሚዎችን በአንድ ወገን በሌላው ወገን ከአላማቸው በመነጨ የአንድነት ጎራውን መጠናከር የማይፈልጉና የሚያስፈራቸውን የጎሰኝነት መንፈስና የሻቢያን አላማ ተሸካሚ የሆኑ ቡድኖችን አካቶ በእነዚህ ሐይሎች የሀሳብ የፕሮፖጋንዳና የሎቢ ሥራዎች እየታገዘ ከውስጥና ከውጪ በሚፈስለት ፈሰስ በከፍተኛ የገንዘብ ሃይል ለማፈራረስ የሚንቀሳቀስ ቡድን ነው።

አደራጃጀቱም ቢሆን ዓላማና ሕልሙን የትግል ስልቱንና አደረጃጀቱን በግልጽና በይፋ በአማራጭነት በማቅረብ ሕብረተሰቡን ኣሳምኖ በፈቃደኝነት የሚያደራጅ ሳይሆን በተደራጁ ፓርቲዎች ክፍሎችና ስብሰቦች ውስጥ ሰርጎ በመግባት በገንዘብ በመንደር ልጅነትና በአሉባልታ የተጠናከረውን ዋርካ በመነቅነቅ የተንጠባጠበውን ሰብስቦ የሚሮጥ ሲሆን ይህ የሚያሳየው ደግሞ እውቀት ራዕይ ጽናትና ለፍቶ ደክሞ የመገንባት ብቃትና ድፍረት ማጣትን ብቻ ሳይሆን እፍራሽና መሰሪ መሆኑን ነው።

2. የሃገር ቤቱ አንጃ ክንፍ.....ከውጪው ከዋና አካሉ ተከፍሎ ወደ ሀገር ቤት ክንፉን የዘረጋው ቡድንም እንደ አባቱ በተመሳሳይ ሥራ የተጠመደ ሲሆን ከሕዝብ ቅንጅት ከፓርላማ አባላት ከተመስገንና ከእገሌ የዚህን ያህል ሰው ቦጭቄና አስጥዬ ወስድኩኝ ከእገሌ ጋር ተለጥፍኩኝ ደብዳቤ ፅፌ ላልፋታ በተክሊል ተጋባሁ በማለት እንደድርቶ የተለያዩ መልኮችን ለጥፎ ከመልበሱ ውጪ አላማና ፅናት ኖሮት ቆላ ደጋውን ወጥቶና ወርዶ ጠልቶ ገብቶ ማደራጀት የሚጠይቀውን ውድ ዋጋ ለመክፈል ቀበቶ ላልቶበት ከፓርላማና ከቤተመንግስት ዙርያ ከመሽከርከር ርቆ መሄድ ያልቻለው የሃገር ቤቱ ክንፍ በሆድ አሳቢ ፍጡራን ግለሰቦችን አሰባስቦ የሆድ አደር መደብና ፓርቲ ለመፍጠር ከመራራጥና የህዝብ ቅንጅትን ለማዳከም ከመውተርተር ውጪ በህብረተሰቡና በአገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች በመግባት ስር በሰደደ መልኩ ሕዝብ ለመብቱና ለነጻነቱ እንዲታገል ትክክለኛ የፓርቲ ስራን የተሞረኮዘ የሚታይ የሚጨበጥና የሚዳሰስ ተግባር የሌለው የኤልያስ ክፍሌና የጋዜጣዊ መግለጫ አንበሳ ነው።

የአንጃው የውጪው አመራርና የሀገር ቤቱ ክንፍ እንዲህ ሆኖ በአፍራሽና በጥፋት ጎዳና እየተጃዘ ሳለ ዲርጊቱን ከዘላቂው የሃገር ጥቅምና ከህዝብ ዴሞክራሲያዊ ግብ

አኻያ ሳይፈትሹ እያዩና እየሰሙ የጥፋት ወገኖችን መደገፍ የባለ ሙብቱ ጉዳይ መሁኑን ብረዳም የሙብቱ አጠቃቀም እውነታና ስልት የተጠቃሚውን ማንነት ይገልጻል የሚለውን ሃሳቤን በማስቀመጥ፣.. በፖለቲካ ስራ ላይ የተሰለፈ ምሁር የወገኑን ኑሮና ሕይወት በመኖር በሕብረተሰቡ ውስጥ የአስተሳሰብ ለውጥና እድገት እንዲመጣ የሚጥር ብሎም ሕዝብ ለነጻነቱና ለሙብቱ ተደራጅቶ እንዲነሳ ታግሎ የሚያታግል ታላቁ የወገናችን ሐይል ነው።

ነብይ በአገሩ እንደሚባለው ሆኖ ነው እንጂ የሕዝብ ቅንጅት መለያችንና ጌጣችን የሆኑትን የተለያዩ ቋንቋ ተናጋሪና ባህል ያላቸውን የሕብረተሰባችን ክፍሎች ውስጥ እስከ ታች ገብቶ በማንቃትና በማደራጀት ከአራቱም ማዕዘን በእኩልነት ለሙብት መከበርና በዴሞክራሲ ጥያቄ ዙሪያና ሥር በማሰባሰብ የሀገሩን ሉዓላዊነትና አንድነቱን መጠበቅ በሚያስችለው መልኩ ስልት ቀይሶ በየክልሉ በማደራጀት በትግል ወቅት ሊከፈል የሚገባውን መራራ ዋጋ ከፍሎና እየከፈለ ሕዝብን ለነጻነቱ የሚያታግል የሚጨበጥ የሚታይ የሚዳሰስ የተግባር ውጤት ያሳየ ነው።

አንጃው እንደ ስልት አድርጎ የተነሳው ከአቶ መለስ ስርዓት ጋር መስራትን ነው። ተናግረውም በተግባር አሳይተውናል። ጥያቄው 17 ዓመት ሙሉ የወያኔ ቡድን ሕዝባችንን በረሃብ በድሕነት በበሽታና በደዌ እየቀጣ ሙብቱንና ነጻነቱን በጠመንጃ ረግጦ በብረት ሃይል እየገዛ ሐገር አፍርሶ ታሪክ ክዶና ባንዲራ አዋርዶ የህዝብ ድምፅ ሰርቆና ኮሮጀ ገልብጦ በአጋዚ ጥይት በሕዝብ የደም ጎርፍ ላይ ቆሞ የሚገዛን ጎጠኛና አምባገነን ከሕዝብ ጋር ቆመው ማስወገድ ባለመፈለግ ከወያኔ ጋር መሥራትን መረጡ። ለምን?

ጉዳዩ አቶ መለስና ቡድናቸው ስጋት አለባቸው፣ ለጭንቀታቸው ሽፋን ሰጪ መከታና ጠበቃ የሚሆንላቸው ሃይል ይፈልጋሉ፣ ቀድሞ የነበሩት ለስላሳ ተቃዋሚዎችና የፓርላማ አባላቶቹ እያስገመገመ የመጣውን የሕዝብ ተቃውሞና ትግል ሊመክቱላቸውና ሊጠብቃቸው አላቻሉም።

ስለዚህ ወያኔ ከሥጋት ለመዳን ጠንካራውን የሕዝብ ቅንጅትን የሚያዳክምለት አዲስ ሐይል ማግኘት ይፈልጋል።

አቶ መለስ የሚያስፈራቸውና የሚያሳስባቸው ጉዳይ የሀገርና የታሪክ ክህደት አይደለም፣ ባንዲራችንን ጨርቅ ነው ስላሉና አህያ አልብሰው በፍጡራ ተምሳሌነት የእኛን ምንነትና ማንነት ስለነገሩን አይፈሩም፣ አፍኖ በመግደልና በአጋዚ ስራዊት በአደባባይ ረሽኖ መረፍረፍ ምንም ማለት አይደለም፣ ስጋታቸው፣አቶ መለስና ጭፍሮቻቸው ላስቲክ ጫማ ገድግደው ቁምጣ ሱሪ አጥልቀው ብረት ተሸክመው ዱዴ ሳንቲም ሳይኖር በኪሳቸው በጠመንጃ ሀይል ሀገራችንን ከወረሩ በሓላ በምርኮኝነት መልክና በኢፍትሃዊና በአድሎ መንገድ የሃገሪታን ሀብትና ንዋይ በመዝረፍ

እራሳቸውንና የጎጥ ጭፍሮቻቸውን ትላልቅ ቱጃሮች አድርገዋል፣ ዛሬ ከጉልት ገበያ መደብ አንስቶ አስመጪና ላኪ ባንክና እንሹራንስ ኮንስትራክሽንና ህንጻ መገናኛና ትራንስፖርት ወ.ዘ.ተ. እና ሌሎችንም ተቆጣጥሮ በእጁ ያስገባውን ትናንት ጸጉሩን አንጨብርሮ ሽርጥ ጠምጥሞ የገባው ጀሌ እስከ አለም ፍጻሜ ቀንና ሌሊት ቢፈጋ ሊያገኝ የማይችለውን ሃብትና ንብረት ይዛል፣ ይህን ይዞ መቀጠል ስለሚፈልግ ሃብት አስጠባቂ ሃይል ይፈልጋል። ከአቶ መለስ ጭንቀትና ስጋት አካያ የዶክተር ብርሃኑ ነጋ አንጃ  ባለማወቅም ሆነ አውቆ ለወያኔ በሎሌነት ጥብቅና ቆሞ በማገልገል ላይ ይገኛል።

በአብሮ መስራትና በመቻቻል ስም በህዝባችንና በሃገራችን ላይ የደረሰን ጥፋትና የወያኔ መሪዎችና ጭፍሮቻቸው የዘረፉትንና የሰረቁትን የህዝብ ሃብትና ንብረት እንደያዙ እንዲገዙን አሊያም ዘርፈው የከበሩበትን ሃብት የሚያስጠብቅላቸው የሆድ አሳቢና ራዒይ አልባ የሆዳም ግብስብስ ሰብሰበው ለማደራጀት ለሚያደርጉት ጥረት አንጃው ለዚህ ጉዳይ የተፈጠረና የተመቻቸ በመሆኑ ግዳጅ ተቀብሎ የህዝብን ትግል በማዳከምና በመጎተት የእድሜ ሥራውን እየተወጣ ነው፣ ይኸውም

1. በሃገራችን የፖለቲካ አየር ውስጥ አንጃው የውሸት ፕሮፓጋንዳዎችን የማይተገበሩ አመለካከቶችንና የስም ማጥፋት ክሶችን በማሰራጨት በህበረተሰቡ አስተሳሰብና የትግል እይታ ላይ ብዥታ ጥርጣሬና ማደናገር ፈጥሮ የአንድነቱን ሃይል ጥንካሬ ማላላትና መፍታትን ከተግባራቱ አንድ አካል ሲሆን

2. የነጩን አለም በሚስብ መልኩ በመቅረብ የአንድነትና የዴሞክራሲው ጎራ የሆነው ቅንጅት ሐገር ወዳድና አክራሪ ሓላ ቀር የሆነ አስተሳሰብ ያለውና የሚያራምድ ዘመናዊና የሰለጠነ ፖለቲካ የማይገባው እንደሆነ አድርጎ በመናገርና በማንጸባረቅ ለአቶ መለስ ጠበቃና አፍ በመሆን የውጪ ሃገራት መንግስታትና ማህበረሰብ ከፖለቲካና ከፍላጎታቸው አካያ ቅንጅትን በስጋትና በጥርጣሬ እንዲመለከቱት ማስደረግ፣

3. ከወያኔ ጋር በሰላም  አብሮ መስራትንና የመቻቻል መንገድን እንደሚያራምድ ለአለም አቀፍ ህብረተሰብና ማህበራት በመግለጽና በማሳየት የአንድነትና የዴሞክራሲ ጎራውን ነጥሎ ብቻውን በማስቀረት በሁሉም አቅጣጫ እንዲመታ በተጠና በታቀደና በረቀቀ ስልት እየሄደ እውንውተኛውን የህዝብ ትግል ለማኮላሸት ሌት ተቀን እየሠራ ያለ አንጃ ነው።

ከአስተሳሰቡ በመነጨና ከአሰባሰባቸው ክፍሎች ማንነትና ፍላጎት በመነሳት የተከተለው መንገድ ከሕዝባችን ኑሮና ህይወት አኻያ ስንፈትሸው ከአፈጣጠሩ ጀምሮ እስከ ዛሬ የሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች ሁሉ ሕዝብ ውስጥ ገብቶ ህዝብን ይዞ ለነገው ብሩህ ተስፋ በመታገል ትግሉ የሚጠይቀውን ጽናትና ውድ ዋጋ ከፍሎ

ወገንን ለነጻነት የሚያበቃ ምሁራዊ ራእይና ባህሪ የተላበሰ የሀገርና የህዝብ የባለ አደራነት ስሜትና አካሄድ የተከተለ ሳይሆን ተጠልፎ የጨነገፈ የወያኔ አገልጋይ ነው።

ይህ የአምባገነን ስርአትን የሚያጠናክር በሆድ የማሰብ... አመለካከት የተጠናወተው.. የዘቀጠና የደኸዬ .. አስተሳሰብ የተሸከመ .. ሀቅ.. እውነውትና..የህሊና ነጻነት የከዳው ልፍስፍስ ተንበርካኪ ሲሆን ያሰባሰባቸው ግለሰቦች ከተክለ ሰውነታቸው ውጪ የተሸከሙት አላማ በደርግ ዘመን ተፈልፍሎ በወያኔ ስርአት ፋፍቶ ያደገውና የህብረተ ሰባችንን አንዱን ክፍል እንደ አራሙጃ አረም በመውረር ስሩን በመሰደድ ላይ የሚገኘው የሆድ አሳቢነት እንሰሳዊ ባህሪ ተላብሰው እኔ ከሞትኩኝ ሰርዶ አይብቀል እንዳለችው ፍጡር በታጋይነት ስም የህዝበን ትግል በመሸጥ የደሃ ወገናችንን ደም እንደ መቿገር መጠው መሰባትና መክበር የለመዱ እኔ ደልቶኝ ተንደላቅቄ ከኖርኩኝና ሐብት ካካበትኩኝ ስለሌላው ወገንና ህዝብ ምን አገባኝ የሚል የሆዳም ግለኛ ስብስብ ነው።

በስራ ለፍቶና በውጤት ከመኖርና ከማደግ ይልቅ ጭራቅ አምባገነኖችን በመጠጋትና በመለጠፍ በፖለቲካ ድጎማ ወይም ፈንድ እራሳቸውን ማኖርና ማደለብ የለመዱ የሆድ አሳቢ ቫይረስ ተሸካሚና አስተላላፊ የሆኑትን ስብስቦና ሽርክና ፈጥሮ ትግሉን ለማደቀፍና ለሆዱ የሚታገል ነው፣ ይህ በምሁራዊ እሴት ራእይና ሞራል የተራቆተ የከርስ አሳቢዎችና የትቅም አላሚ ፍጡራን አንጃ በህገራችን የፖለቲካው ድባብ ውስጥ ቦታ አግኝቶ በዚህ በነቀዘ አላማና አስተሳሰብ ተሰባሰቦና የሆድ አደር መደብ ወይም ቡድን በመፍጠር የፖለቲካው ምህዋር ለመቆጣጠር የሚያደርገውን የኢንፋቂቅት ጉዞ በአመለካከትና በህዝብ ራእይ ካልተቃወምነውና ካልታገልነው ከተሸከመው ባዶና የዘቀጠ አስተሳሰብ ባሻገር አንጃው ከጀርባውና ከጭራው በህዝባችን አንድነትና ህይወት በትግላችንና በሉኣላዊነታችን ላይ ከጀርባው አደጋና መዘዝ ያስከተለ ስለመሆኑ ፍንጨችና ምልክቶች እየታዩ ስለሆነ የሀገራችን ችግር ጅራቱ የረዘመ ከባድ አደጋ እንደተጋረጠብን የሚያሳይ ነው።
የዚያቺን ፍጡር አስተሳሰብና ስሜት በመጋራቱ ብቻ ሳይሆን ልንታገለው የሚገባን የሀገር ጉዳይን ጨምሮ የያዘ በመሆኑ በአጽኖት እንድንታገለው እያሳሰብኩኝ ወደ ሌላ ሃሳብ ስገባ አንጃው መፈክር መሰል አባባሎች ሲኖሩት ይሐውም አብሮ መስራትና መቻቻል በማለት የሚያንጸባርቀው ነው።

በ21ኛው ክፍለ ዘመን ወያኔዎች ተጠራርተው ከተራራ አናት ላይ ወርደው ሃገራችንን በመውረር ስልጣንን ተቆጣጥረውና ሕዝብን በጎሳ ከፋፍለው በረሃብ በድህነት በበሽታና በደዌ ወገናችንን እየቀጡ በበረት የሚገዙ ሽፍቶችን የህዝብን ውሳኔና ፈቃድ አግኝተው የሚያስተዳድሩ እንዳልሆነ እያወቁ እንደ ጥሩ ስርአት አድርገው በማቅረብ ሊያሳምኑን መቃተታቸውን ስናይ ወያኔ ከውሸትና ከፕሮፓጋንዳ ባሻገር የዴሞክራሲ ጽንሰሃሳብ ያልተጠረበት ዘረኛ ቡድን መሆኑን

እየተረዱ ምንም አይነት የመብትና የነጻነት ተስፋ ባልበቀለበት ምድረበዳ ሀገር ለመብትና ለነጻነት ታግሎ ስርአቱን ከመለወጥ ውጪ እንዴት ሆኖ ነው ከገዳይ ጎጠኛ ለፍርድ ቀራቢ ጋር አብሮ መስራት የሚቻለው።

መቻቻልና አብሮ መስራት ሊተገበር የሚችለው ህዝብ በውሳኔው ፈቅዶ የሚቆጣጠረው የራሱን መንግስት ሲመሰርት ያኔ ተነስተን በአመለካከትና በህዝባዊ አላማ ልንታገለው የሚገባን አንዱ የትግል ዘርፍ ነው።

ወገናችን ቀሞ የሞተውና ሕይወቱ ከወለል በታች ወርዶ በተፈራረቀው የብረት አገዛዝ ስር በመማቀቅ ደስታ ብቻ ሳይሆን ተስፋ ርቆት የመክውራ ሕይወት የሚገፋው ዋንኛው ምስጢር ለአርሱና ለህገሩ የቆመ ጠንካራ ሕዝባዊ ራእይ ያለው ድርጂት መፍጠር ያለመቻላችን ነው።

ስለዚህ በጽናታና በጥንካሬ ቆመን ይህንን የሕዝብ ሃይል የሆነውን ቅንጅት ካላጠናከርነውና ካልጠበቅነው ሀገራችንም ሆነ ሕዝባችን ጥያቄ ምልክት ውስጥ እንዳይገቡ እሰጋለሁ።

**ጉልቻ ቢቀያየር ወጥ አያጣፍጥም!!**
**ሊነጋጋ ሲል ይጨልማል!!**

**ኢትዮጵያ በእግዚአብሔር እርዳታ በልጆቿ ትግል ታሸንፋለች!!**